

ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ
የከፍተኛው መ/ት/ቤት ም/ዲን

# ፭ቱ የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያን።

«ኦርቶዶክስ የተሰኘው ቃል ከሁለት የግሪክ ቃላት ተገናኝቶ አንድ የሆነ ቃል ነው ። «ኦርቶ» ርቱዕ (የቀና) «ዶክሳ» ሃይማኖት ማለት ሲሆን «ኦርቶዶክስ» የቀና ፣ ቀጥ ያለ ሃይማኖት ማለት ነው ።

በግእዝ ልሳን «ርትዕት ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ፡የአባቶቻችን ሃይማኖት የቀናች ፣ ቀጥ ያለች ናት»የሚል ቃል በቅዱሳት መጻሕፍት ይነበባል ፤ በዚህ ስያሜ በምሥጢረ ሃይማኖት ትርጉምና በይዘቱ በመለያየት ከሁለት የተከፈሉ አብያተ ክርስቲያን ይጠቀሙበታል ። እነርሱም የኦሪየንታል (የምሥራቅ) አብያተ ክርስቲያንና የግሪክን ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ናቸው ።

የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን የሚለዩት «የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያን» በመባል ነው፤እነዚህም አብያተ ክርስቲያን ከዚህ ቀጥሎ የተ መለከቱት ናቸው ።

፩/ የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣
፪/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣
፫/ የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣
፬/ የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣
፭/ የሕንድ (ማላባር) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣

እሊህ አምስቱ የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ) አብያተ ክርስቲያን፣ ከሌሎቹ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚለዩ ፣

በምንስ እንደሚገናኙ ለገጸ ንባብ የሚያበቃ ሰፋያለ ዓምድ ስናገኝ እንጽፋ ለን።በዚች አነስተኛ መጽሔት ግን አብያተ ክርስቲያኑ የተመሠረቱበትን ዘመንና ሥፍራ ለማመልከት ያህል ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል አቅር በናል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፩/ የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፤

የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በመጀመሪያው ምእት ዓመት በዘመነ ሐዋርያት ነው መሥራቿም ከሰብዓ ሁለቱ አርድእት አንዱ የሁለተኛው ወንጌል ጸሓፊ ቅዱስ ማርቆስ ነው ።

በእስክንድርያ በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ የተመሠረተች መሆኗን አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት አረጋግጧል፡(Eusebius 11E.II.16)

እስክንድርያ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከፍ ብለው ከታዩት ከአንጾኪያና ከሮም መንበረ ሊቀ ጵጵስና ጋር ዕሪና ያላት ከፍተኛ ቤተክርስቲያን ናት። መንበረ ፓትረካናው ወደካይሮ ተዛውሯል ።የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ከፍተኛ ፈተናና ስደት ደርሶባታል በሦስተኛው ምእት ዓመት የምንኵስና ሥርዓት በቅዱስ እንጦንስና በሌሎችም አበው በግብጽ ተጀመረ ፤ ገዳማት ተመሠረቱ ፤ በምድረ ግብጽ የተጀመረው ክርስቲያናዊ የምንኵስና ሥርዓት ክርስትናን በተቀበሉ ክፍላተ ዓለም ሁሉ ተስፋፋ ።

የግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክና ከሌሎችም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን የተለየችው በ፬፻፶፩ ዓ/ም በተደረገው የኬልቄዶን ጉባኤ ሲሆን፡በዚያን ጊዜ መሪዋ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ነበር ።

ኮፕቶች ቅብጦች በ፮፻፲፮ በፋርስ ኃይል ስር ወድቀው እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል ። በ፮፻፵፪ በዐረቦች ተወረሩ፤ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስልምና ሃይማኖት የበላይ ሆኖ በክርስቲያኖች ላይ ታላቅ ችግር ደርሶባቸዋል።በተለይም ካሊፍ አል ሐኪም በተባለው እስላማዊ መሪ ከ፱፻፺፮—፩ሺሕ፳፩ ከፍተኛ መከራና ችግር ደርሶባቸዋል፤፫ሺሕ አብያተ ክርስቲያንን አፍርሶባቸዋል፤ የግብጽ ክርስቲያኖች ትክክለኛውን ነጻነት ያገኙት እንግሊዞች ግብጽን የቅኝ ግዛት በአደረጉበት የቴሌስ ከቢርን ጦርነት በአስተከተለው በ፲፰፻፹፪ ወቅት ነበር። በአሁኑ ጊዜ የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ብቻ እንደሆኑ በታሪክ ተመዝግቧል ።

በውጭ አገር ያሉትን ምእመናን ጨምሮ ስድስት ሚሊዮን እንደሚሆኑ ይገመታል፤በአሁኑ ጊዜ አንድ ፓትርያርክና ስድሳ ጳጳሳት አንድ ሺህ አምስት መቶ ቀሳውስት አንድ ሺህ ሁለት መቶ አብያተ ክርስቲያን እንዳሏቸውየታሪክ መዝገብ ያስረዳል ።



በተጨማሪም በውጭ አገር በኢየሩሳሌም ፣ በሱዳን ፣ በደቡብ አፍሪቃና በኬንያ መንበረ ጵጵስና አላቸው።በኢትዮጵያ ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት በጵጵስና ፣ ደረጃ መሪዎች ሆነው ከቀዩ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷን መሪ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም መርጣ መሾም በመቻሏ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበራቸው የበላይነት አክትሟል ።

## ፪/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት «ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ በብዙ ሥፍራ ይገኛል ።

ለምሳሌ «የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው ፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል » (ዘፍጥረት ፪ ፡ ፲፫)

«ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች »

(መዝሙረ ዳዊት ፷፯/፷፰/፴፩)

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው ቀደም ብሎ በዘመነ ሐዋርያት ታላቅ ባለሥልጣን በነበረው በሕጽዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ አማካይነት ነበር ። (የሐዋርያት ሥራ ፰.፳፮—፴) በአራተኛው ምእት ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በሲኖዶስ ደረጃ ከፍ ብሎ ፍሬምናጦስ የተባለው አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተብሎ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ ሆኖ ተሾመ፤እርሱም ብዙዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሌሎች ልሳናት ወደግእዝ ቋንቋ ተርጉሟል ።

በአምስተኛው ምእት ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በኋላ የኬልቄዶንን ጉባኤ የተቃወሙ ዘጠኙ ቅዱሳን ሶርያውያን መነኮሳት ከቢዛንታይን በስደት ወደኢትዮጵያ መጡ ።

ወደኢትዮጵያ መምጣት የመረጡትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶንን ጉባኤ ከተቃወሙት መካከል አንዷ በመሆኗ ነበር ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስድስተኛውና በሰባተኛው ምእት ዓመታት የሃይማኖት ሥነ ጽሑፍን በእጇጉ አስፋፍታ ነበር ። ነገር ግን በሰባተኛው ምእት ዓመት በቀይ ባሕር አካባቢ የእስልምና እምነት ብቅ አለ፤ሆኖም ኢትዮጵያን ሊደፍር አልቻለም ። በዓለም የታወቁና የተደነቁ ፣ በጸላእት ከድንጋይ የተፈለፈሉ ዐሥራ ሁለት አብያተ ክርስቲያን በላስታ ታነጹ ። በዐሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክፍለ ግዛት«ግራኝ መሐመድ»የሚባል አምባ ገነን



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን ጠላት ተነሥቶ ብዙዎች አብያተ ክርስቲያንን አቃጠለ። መጻሕፍት ቅዱሳትን ቈንነጻጸለ፤ብዙም ጥፋት አደረሰ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቋቋመውና ርሱ ከነጠሩ ተመደሰሰ ። አብያተ ክርስቲያን ታደሱ ፤ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሥርዓት ወደ ጥንት ክብሩ ተመለሰ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር የተዋሐደ ሥጋና ደም በመሆኑ ኢትዮጵያን የሚፈታተኑ ጠላቶች ሁሉ እርስዋንም ፈትነዋታል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጵጵስና ማዕርግ ደረጃ ለአያሌ ዘመናት በግብጽ መንበረ ፓትረካና ስር ስትተዳደር ቈይታ ከ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ጀምሮ ከልጆቿ ሊቃውንት ራሷ መርጣ ጳጳሳትን ለመሾም በመብቃቷ በአሁኑ ጊዜ በተቀደሰ አመራር የሚመሯት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሦስተኛው ፓትርያርክ ናቸው ።

በአሁኑ ጊዜ ፴፪ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ያሏት ሲሆን በመንፈስ ቅዱስና በሥርዓተ አበው የጠነከረ ቅዱስ ሲኖዶስ አላት። በአገር ውስጥ ዐስራ ስድስት አህጉረ ስብከት (መናብርተ ሊቀ ጵጵስና) ያሏት ሲሆን፣ በውጭ አገር በኢየሩሳሌም በምዕራብ አህጉር ፣ በሱዳን ፣ በጂቡቲ ፣ በምዕራብ ጀርመንና በኬንያ በሊቃነ ጳጳሳት መንበር ደረጃ መንፈሳዊ እድገቷ እያደገ ኼዷል ።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቍጥር ፳፰ሚሊዮን ሲሆን ፪፻፶ሺህ ካህናት ፳ሺህ አብያተ ክርስቲያን አሏት። በጠቅላላው በውስጧ ያሉትን ድርጅቶችና የሥራ ፍሬ በዚች አነስተኛ መጽሔት መግለጽ ስለማይቻል በሚቀጥለው መጽሔት ለመግለጽ አቆይተነዋል ።

## ፫/ የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ።

የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመሠረቱ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በሚባል የታወቀች ነበረች ። ነገር ግን በኬልቄዶን ጉባኤ ጊዜ የጉባኤውን ውሳኔ ባለመቀበሏ የግብጽን የኢትዮጵያንና የአርመንን አብያተ ክርስቲያን ፈለገ ሃይማኖት በመከተልዋ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከሁለት ተከፍላለች ። የስም አጠራሩም የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ መሪዎቿና ምእመናኑ«ያዕቆባውያን»በመባል በመሪያቸው ይጠራሉ። በአሁኑ ጊዜ የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቱርክ የእስልምና ሃይማኖት ደጋፊ መንግሥት ስር በመሆኗ ታላቅ ችግር አለባት፤የምእመናኗ ብዛት ፩፻፵፪ሺህ በብሔር አቀፍ ፫፻ሺህ በመካከለኛው ምሥራቅ ሲሆን፣ ፶ሺህ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ እንደሚገኙ ተረጋግጧል። ቀደም



ብሎ ከ፩ሚሊዮን በላይ የሕንድ (የማላባር) ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በእርሷ አስተያደር ውስጥ ነበሩ፤አሁን ግን ራሳቸውን በመቻል መንበረ ፓትረካናቸውን ስለለዩ የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ቍጥሯ ዝቅ ብሏል፤ሆኖም በጣም ጠንካራ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስታያን መሆኗ በመንፈሳዊ አስተዳደሩ መታወቅ ችሏል።፳፫ መናብርተ ጵጵስና ፴፪ ጳጳሳት አሏት፤ፓትርያርኳም ቅዱስ አግናጥዮስ ዘካ ቀዳማዊ ናቸው ።

## ፬/ የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ።

የአርመን ሕዝብ ክርስትና በመቀበል የመጀመሪያዎቹ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ነው ። የክርስትና ሃይማኖትን በአርመን ያስፋፋው «ትሪዳትስ ሣስተኛ» ተብሎ የሚጠራውን የአርመን ንጉሥ ያጠመቀው የቂሳርያና የቀጳዶቅያ መትሮፖሊት የጵጵስና ማዕርግን በ፪፻፺፬ ድኅረ ልደተ ክርስቶስ የሾመው ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን ነበር ።

ብፁዕ ጎርጎርዮስ የመጀመሪያውንና አሁንም ያለውን መንበረ ሊቀ ጵጵስና በአራራት ተራራ በስተሰሜን በኩል በሚገኘው በኢቸሚአዚን አቋቋሙ። በ፫፻፺፯ ዓ/ም እንደ አውሮፓ ዘመን አቈጣጠር አርመን በቢዛንታይንና በፋርስ መንግሥት ከሁለት ተከፍላ ነበር፤ በ፩፪፴ ዓ/ም የንጉሣቸው ወደቀች፤ ተከፋፈለች ። ይሁን እንጂ ዘራቸውን ቋንቋቸውን ፣ ሥነ ጽሑፋቸውንና ሃይማኖታቸውን በጥንቃቄ ጠብቀው ፈተናውን በመታገስ ኖረዋል ።

አርመን በአሁኑ ጊዜ በሶቬዬት ኅብረት ዐስራ አምስተኛዋ ሪፐብሊክ ስትሆን፣የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ከአርመን ዋና ከተማ የሬቫን ወጣ ብሎ በሚገኘው የኢቸሚአዚን ገዳም ውስጥ ነው ።

የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአርመን ሁለት ሚሊዮን ተኩል ሲሆኑ፣ በውጭ አገሮች በኢጣሊያ በኢየሩሳሌም ፣ በለንደንና በአሜሪካ በሌሎችም ሥፍራዎች ይገኛሉ። በተለይም በሰሜን አሜሪካ ፩፻ሺህ አርመናውያን ክርስቲያኖች ይኖራሉ። በኢየሩሳሌም የሚገኘው ሊቀ ጵጵስናቸው በጣም የታወቀ ነው። በሶቬዬት ኅብረት አምስት መንበረ ጵጵስና አምስት መቶ አብያተ ክርስቲያንና ገዳማት አምስት መቶ ጳጳሳትና ቀሳውስት ይገኛሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

በአሁኑ ጊዜ የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሪ የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የኢየሩሳሌምና የቍስጥንጥንያ መንበር ካቶሊክስ (እንተ ላዕለ ኵሉ) በመባል የሚጠሩት ቅዱስ ባዝጌን ቀዳማዊ ናቸው ።

<u>፭/ የሕንድ (ማላባር) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ።</u>

የማላባር ክርስቲያኖች የተሰኘው ስያሜ በደቡብ ሰሜን የሕንድ ግዛት በካራላ የሚገኙ ክርስቲያኖች የሚጠሩበት ነው ። በተለይም «የቅዱስ ቶማስ ክርስቲያኖች» በመባል የታወቁ ናቸው ።

የክርስትና ሃይማኖት በዘመነ ሐዋርያት ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በአንዱ በቅዱስ ቶማስ አማካይነት የተጀመረ መሆኑ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የታወቀ ነው ። ቅዱስ ቶማስ በሕንድ የክርስትና ሃይማኖትን ሲያስፋፋ በሰማዕትነት ሕይወቱን ሰጥቷል ።

እንዲህ ለመሆኑም በሰባተኛው ምእት ዓመት የተገኘው በመስቀል ላይ የተቀረጸው ቃል ማስረጃ መሆኑ ተጽፏል ።

ከመሠረቱ ከምሥራቃዊት ሶርያ የመጀመሪያዎቹ የክርስትና እምነት ተከታዮች ወደ ሕንድ ኺደው እንደነበርና የክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት እንደቻለም ይተረካል ። ጳጳስ የሚላክላቸው ከሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ ግን የራሳቸው ፓትርያርክ «ካቶሊክ» (እንተ ላዕለ ኵሉ» በሚል የክብር ቅጽል የሚጠራ አላቸው፤ ይሁን እንጂ የሶርያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረካና የበላይነት በአክብሮት አንጻር ይቀበላሉ ። የምእመናኑ ቍጥር አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ሲሆን ዐሥራ አምስት መንበረ ጵጵስና አንድ ሺህ አንድ መቶ ሠላሳ አብያተ ክርስቲያን ፡ ዐሥራ አምስት ጳጳሳት ፡ ዘጠኝ መቶ አምሳ ቀሳውስትና ስድሳ ሁለት ዲያቆናት አሏት ። ቤተ ክርስቲያኒቱ የተመሠረተችው በ፶፪ ዓመተ ምሕረት ነው ። ሆስፒታል ፡ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆችን አቋቁ ማለች ።

የዚች ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆኑ ክርስቲያኖች በሕንድ በከፍተኛ ደረጃ የተማሩና በአፍሪቃ ከፍተኛ ሐዋርያዊ ተልእኮን ያጠናከሩ ሲሆኑ በታናሿ እስያ በአብዛኛው ክፍል ሐዋርያዊ ተግባራቸውን በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ ። በተለይም በአሜሪካ በተላቋ ብሪታንያና በምዕራብ ጀመርን አብያተ ክርስቲያን አሏቸው ።



ከዚህ በላይ በአጭሩ ታሪካቸው የተገለጹ አምስቱም የኦሪየንታል (የምሥራቅ) ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ፤ ከሁለት አካል አንድ አካል ሆኖ፤ በተዋሕዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ተወልዶ ያዳነን መሆኑን በአንድነት ያምናሉ ። ስለመንፈስ ቅዱስም «ዘሠረጸ እምአብ» በማለት እንድናቸው ።

ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ይቀበላሉ፤በጸሎተ ቅዳሴ ሊተባበሩ ፡ የጌታን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም አብረው ሊቀበሉና ሊያቀብሉ ይችላሉ ። ከቋንቋና ከንዳንድ ባህላዊ አመራር በስተቀር ልዩነት የላቸውም ።

« ሰዋስወ ብርሃን »

የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

# ዓመታዊ መጽሔት

ቍጥር ፫

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org